# <u>የራሱን ሕዝብ ደጋግሞ የከዳ የወያኔ መንግሥት ።</u>

ከ- አባታቦረ

አፄ ዮሐንስ ሕይዎታቸዉን የገበሩለት፤ሠራዊታቸዉ አጥንቱን የከሰከሰለተ፤ምዕራባዊ ኢትዮጵያ ተቆርሶ ለሱዳን እንዲሰጥ ፤መለስ ዜናዊ አመቻችቶ ሙቷል።ወራሾቹ ኑዛዜዉን ተግባራዊ ለማድረግ በሚሯሯጡበት ሰዓት፤እነሆ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እሮሮዬን አቀርባለሁ።

*በደም ተለሰና በአጥንት የታጠረዉ*
*ሱዳን ሳይፈጠር እንግሊዝ የሚያዉቀዉ*
*ቋሚ ነዉ ድንበሩ ጊዜ የማይሽረዉ።*

*የወያኔ መሪ ዛሬም ከመቃብር ከፍ አርጐ ይጮሃል*
*ኢትዮጵያ ሳትጠፋ እሱ በመጥፋቱ በጣሙን ይቆጫል*
*በዚህም መንስኤ ጉዳይ አስፈጻሚ አግዓዚን አቁሟል*
*እነ ኃ/ማርያም ለሞተ መታዘዝ እድላቸዉ ሆኖአል።*

*መለስ በቁም ሳለ ለሱዳን ወዳጁ ቃል የገባዉን*
*የኢትዮጵያን ለም መሬት ዉሀ ገቤዉን*
*ሁመራ የደካ እስከ አሶሳ ድረስ የተዘረጋዉን*
*ተሰንጥቆ እንዲሰጥ አቶ መለስ አዟል*
*በሞት ቢወሰንም የወያኔ መንጋ ተግባራዊ ያረጋል።*

*ሀገር ሲቸበቸብ ባሕር በር ሲዘጋ መቸ ሀግ ! ተባለ*
*በእዉነት በዉስጣቸዉ እንደሱ ያለ ሰዉ አይን ያለዉ ነበረ ?*
*መለስ ክፉ ባንዳ በአባቱ አጥንት የማለ*
*ኢትዮጵያን ለማጥፋት ያላወላወለ*
*በዚህ በእኛ ዘመን አራሙቻ ሆኖ በድንገት ብቅ ያለ።*

*በደቡብ መተማ ማህበረሥላሴ ግዛት*
*ሽንፋና ማጠቢያ አስከኒት ገላባት*
*ሰሜናዊ መተማ ወዲነብሮ ፤ ግራርዉሀ፤ ዋ ! ሽመለጋራ*
*የሱዳን ክልል ተብሎ በወያኔ ሲጠራ*
*ከእንግዲህ ወዲህስ ምን ብለን እናዉራ ።*

አርማጭሆ እሪ ! ብለህ ንገር ለጠገዴ
ጠገዴ እሪ !ብለህ ንገር ለወልቃይት
ወልቃይት እሪ ! ብለህ ንገረዉ ለቋራ
ዳግም እንዲወለድ ፤
ዳግማዊ ቴዎድሮስ ሀገር እሚመራ።